DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS



www.dcps.dc.gov

ጥያቄዎች አሉዎት? በቀጣዩ አድራሻ ያግኙን
(202) 719-6613 ወይም ofpe.info@dc.gov.

1200 First Street, NE, Washington, DC 20002

/dcpublicschools @dcpublicschools @dcpublicschools

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የወላጅ ስርዓተ ትምህርት መምሪያ



# የክፍል ደረጃ 4



## የወላጅ ስርዓተ ትምህርት መምሪያ የአጠቃቀም መንገድ፣

ይህ መምሪያ ልጅዎን በቤት ውስጥ ለማገዝ የሚያስፈልጉዎትን መሳሪያዎች ይሰጥዎታል። በዚህ የመረጃ ጥራዝ ውስጥ፣ ልጅዎ የትምህርት ግቦቹን እንዲያሳካ ለማገዝ እንዲችሉ በ DCPS ስርዓተ ትምህርት ላይ የተመሰረቱ ስትራቴጂዎችን ያገኛሉ። ልጅዎ በት/ቤት ውስጥ የሚማረውን ትምህርት እና በተጨማሪም በቤት ውስጥ እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ጥሩ ግንዛቤ ይጨብጣሉ/ያገኛሉ።

## እርስዎ ማድረግ የሚችሉት፣

በልጅዎ አካዳሚክ ብቃት ላይ እርስዎ ወሳኝ ሚና ይጫዎታሉ። በቤት ውስጥ ጥሩ ትምህርት እንዲያገኙ ለማድረግ እነዚህ የተወሰኑ አስፈላጊ ነጥቦች ናቸው፡

- ትምህርት የስኬት መሰረት መሆኑን ልጅዎ እንዲያውቅ ያድርጉ።
- ልጅዎ 4ኛ ክፍል ውስጥ ምን ይማራል ተብሎ እንደሚጠበቅ ይወቁ።
- ልጅዎ ከፍተኛ የሆኑ የአጭር ጊዜና የረዥም ጊዜ አካዳሚያዊ ግቦችን እንዲያሰቀምጭ ያግዙት።
- የቤት ስራ በተገቢው ሰአት እና በአግባቡ እንዲያጠናቅቅ በቂ ጊዜ ይስጡ።
- በት/ቤት ውስጥ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ከልጅዎ ጋር በመነጋገር ሒደታዊ ለውጦችን ያለማቋረጥ ይከታተሉ።
- ለልጅዎ ይሟገቱ።
- የልጅዎን ጥንካሬ ከመምህሩ ጋር ይጋሩ።

## የልጅዎን መምህር መጠየቅ የሚያስፈልጉ ጥያቄዎች፣

ከልጅዎ መምህር ጋር በሚወያዩበት ጊዜ ስለ ልጅዎ የትምህርት አቀባበል እና ሁኔታ ላይ ትኩረት እያደረጉ ቀጥሎ የተመለከቱትን ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡

- የመማር ግቦች ምንድን ናቸው? የመማር ግብ አስመልክቶ ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች እንደ ምሳሌ ሊነግሩኝ ይችላሉ?
- የልጄን ስራ እንደ ምሳሌ ማየት እችላለሁ? እነዚህን የመማር ግቦች የሚያሳካው ወይም የማያሳካው እንዴት ነው?
- ልጄ በትምህርቱ እያለ/ ከሆነ ደረጃ በላይ ሲዘልቅ ሌላ ተጨማሪ ድጋፍ ማድረግ የሚገባኝ ምንድናቸው? ቤት ውስጥ ምን ማድረግ እችላሁ?
- ቤት ውስጥም መተግበር ያለባቸው የመማሪያ ክፍል ውስጥ መደበኛ ተግባራት ምንድን ናቸው?
- የእርስዎን ክፍለ ጊዜ በተመለከተ ለልጄ በየቀኑ ማቅረብ ያለብኝ ጥያቄዎች ምን ዓይነት ናቸው?

## ከልጅዎ ጋር መነጋገር፣

ጥሩ ጭውውቶች ልጆቻችን በሕይወታቸው ውስጥ እኛ እንደሚያገባን እንዲያዩ ያግዛሉ። እነዚህ ከልጆችዎ ጋር መልካም ውይይት በሚያደርጉበት ጊዜ በቅድሚያ መጠየቅ የሚያስፈልጉ ጥያቄዎች፡

- እስኪ በቀንህ ውስጥ ምርጥ ስለምትለው ጊዜ አውራኝ።
- በውሎህ ውስጥ ያጋጠመህ እጅግ በጣም ፈታኝ ነገር ምንድነው?
- ዛሬ ከተማራችሁት ውስጥ አንድ ነገር ልታሳየኝ ትችላለህ?
- ት/ቤት ውስጥ የምታነቡት መፅሐፍ ምንድን ነው? የምትወደውን መገለጫ ባህርይ ብትነግረኝ? ይህን መገለጫ ባህርይ የምትወደው ለምንድን ነው?
- በት/ቤት ውስጥ ከዚህ በላይ መስራት አለብኝ የምትላቸው ነገሮች ምንድናቸው? በአነስተኛ መጠን ማድረግ አለብኝ ብለህ የምታስበውስ ምንድን ነው? ለምን?

# የአራተኛ ክፍል ተማሪዬ እየተማረ ያለው ነገር

| | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት | ሒሳብ | ሳይንስ | ማህበራዊ ሳይንስ |
|---|---|---|---|---|
| የበልግ ወቅት | ተማሪዎች ስለ ቅድመ ኮሎምቢያና አሜሪካ፣ ስለ አሰሳ እና ስለ ዩናይትድ ስቴትስ ቅድመ አሰፋፈሮች ይማራሉ። ከተለያዩ ፅሑፎች የሚያገኙትን መረጃ አነጻጽረው በመተንተን በቅድመ አሜሪካ አሰፋፈሮችና እዚያ በኖሩ ሰዎች መካከል ንጽጽሮችን ያካሂዳሉ። ታሪካዊ መረጃዎች የተጻፉበትን መንገድ ከግምት ውስጥ በማስገባት ታሪካዊ ትርክትን ይገዳደራሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች የደራሲያንን ሕይወት በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎችን ያነብባሉ፣ የፈጠራ ስራዎቻቸውን ናሙናም ያያሉ። የደራሲ ቅርስና የሕይወት ተሞክሮዎች ማንነታቸውነ እንዴት እንደሚቀርጻው ይማራሉ። የአንድ ሰው ማህበረሰብ፣ የሕይወት ተሞክሮዎችና ቅርስ ማንነታቸውን እንዴት እንደሚቀርጻውና በአጻጻፍ ዘይቤያቸው ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድር ለማሳየት ከተለያዩ ጽሑፎች የተገኙ መረጃዎችን እንዴት እንደሚተነትኑ ይማራሉ። | ተማሪዎች የመደመር እና የመቀነስ የቃል መልመጃዎችን ለማጠጋጋት፣ ለማወዳደርና ለመፍታት የቦታ ዋጋን ይጠቀማሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች የተለያዩ የቦታ ዋጋ ስልቶችን በመጠቀም ባለ ብዙ አሃዝ የማባዛትና የማካፈል መልመጃዎችን ይሰራሉ። | ተማሪዎች የተክልና የእንስሳት ክፍሎችን እና የእንስሳት የስሜት ሕዋሳትን ይዳስሳሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች ኢነርጂ እንዴት ሊተላለፍና ሊከማች እንደሚችልም ይማራሉ። | ሰሜን አሜሪካን በጣም ልዩ የሚያደርጋት ምንድን ነው? ተማሪዎች በተወላጅ አሜሪካውያንና በአካባቢ መካከል ያለውን ተግባቦት ይተነትናሉ፣ ሃይማኖታዊ እምነቶቻቸውንና ከአውሮፓውያን አሰሳ በፊት ጎሳዎች እንዴት ይኖሩ እንደነበር ያጠናሉ።<br>•••<br>ሕይወት በቅኝ ገዥ አሜሪካ ጥሩ ነበር? ተማሪዎች ቅኝ ግዛቶች እንዴት እንደሚፈጠሩና ተቋማትም በጊዜ ሒደት እንዴት እንደተስፋፉ ይዳስሳሉ። |
| የክረምት ወቅት | ተማሪዎች አሜሪካውያን ቅኝ ተገዥዎች ለምን ከታላቋ ብሪታኒያ ነጻ መውጣት እንደፈለጉ ይማራሉ። በአሜሪካውያን ቅኝ ተገዥዎችና በታላቋ ብሪታኒያ መካከል ግጭትና ጦርነተ ያስከተሉትን የ1770ዎቹ አጋማሽ ዋና ዋና ክስተቶችነ በተመለከተ ያነብባሉ። የአንድ ሰው ዕይታ አንባቢ ስለ አሜሪካውያን አብዮታዊ ጦርነት ያለውን ግንዛቤ እና/ወይም አስተያየት እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድርበት ይማራሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች በተፈጥሯዊ ዓለም እና በሰው ልጅ ማህበረሰብ ውስጥ አለትና ማዕድናት ወሳኝ ሚና እንደሚጫወቱ ይማራሉ። በትምህርታቸውም ወቅት አለቶች እንዴት በአለታዊ ኡደት እንደሚፈጠሩና እንደሚቀየሩ፣ አንደዚሁም በሶስት ዋና ዋና ምድብ እንዴት እንደሚመደቡ ይማራሉ፡ ኢግኒዬስ፣ ሴዲሜንታሪ እና ሜታሞርፊክ። አለቶች እንደ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ እሳተ ገሞራ፣ የአፈር መሸርሸርና ቅሪተ አካል ለመሳሰሉ በሰው ልጅ ላይ ተጽእኖ ለሚያሳድሩ ነገሮች እንዴት አስተዋጽኦ እንዳላቸው ይማራሉ። | ተማሪዎች ክፍልፋዮችን ያወዳድራሉ፣ በቅደመ ተከተልም ያስቀምጣሉ። ተማሪዎች በክፍልፋዮች የመደመር፣ የመቀነስና የማባዛት መልመጃዎችን ይሰራሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች ክፍልፋዮችን እንደ ዴሲማል ተረድተው ይጽፋሉ። ተማሪዎች የዴሲማሎችን መጠን በተመለከተ ምክንያት በመስጠት ያወዳድራሉ። | ተማሪዎች ሰዎች የብርሃን ወይም የድምፅ ሞገዶችን በመጠቀም ረዥም ርቀት የሚሸፍን ግንኙነት እንዴት እንደሚያደርጉ ይዳስሳሉ።<br>•••<br>ተማሪዎች ተፈጥሯዊ የመሬት ሒደቶች በሰዎች ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ ለመቀነስ ከአንድ በላይ መልመጃዎችን የማመንጨትና የማነጻጸር ስራ ይሰራሉ። | አብዮቱ አሜሪካን አንድ አደረገ ወይስ ከፋፈለ? ተማሪዎች የነፃነት ዲክላሬሽን ጠቀሜታን ይተረጉማሉ፣ የአብዮታዊ ጦርነት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ መንስኤዎችን ይወስናሉ። |
| የፀደይ ወቅት | ተማሪዎች በጥንታዊ ግሪክ አፈታሪክና በአሁኑ ጊዜ ስላሉ ጀግኖች ታሪክ ይማራሉ። አንድን ሰው ጀግና ሊያሰኙ የሚችሉ የተለያዩ ነጥቦችንና መገለጫ ባህርያትንም ይዳስሳሉ። ተማሪዎች ደራሲያን የአንድን ጽሑፍ ማዐከላዊ መልዕክት ለማስተላለፍ ጀግኖችን የሚጠቀሙባቸውን መንገዶችም ይተነትናሉ ። | ተማሪዎች ማዕዘኖችን ይገነዘባሉ እና ይለካሉ እንዲሁም ይለካሉ። | “ይበልጥ እንከን የለሽ ሕብረት” የምንፈጥረው እንዴት ነው? ተማሪዎች የነጻነት ዲክላሬሽን እና የኮንፌዴሬሽን ሰነዶችን ድክመት ይተነትናሉ፣ ሕገ መንግስቱም እንዴት እንደሚሰራና በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ ዜጎች ላይ ስለሚኖሩት አንድምታዎች ያጠናሉ። | |

# ከአራተኛ ክፍል ተማሪዬ ጋር የማከናውናቸው ተግባራት

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

**በየቀኑ ለ20 ደቂቃ ያህል አብረራችሁ አንብቡ።**

| | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት | ሒሳብ | ሳይንስ | ማህበራዊ ሳይንስ | የማበልጸጊያ ተግባር |
|---|---|---|---|---|---|
| **የበልግ ወቅት** | በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ ቤተ መጻሕፍት በመሄድ በአሜሪካውያን እና አውሮፓውያን ሰፋሪዎች ላይ ሶስት የተለያዩ ጽሑፎችን ያግኙ። እነዚህን የጽሑፍ ምንጮች በማንበብ ስለእያንዳንዱ የመረጃ ምንጭ ተመሳሳይነትና ልዩነት ማስታወሻ ይያዙ። bit.ly/FindMyLibrary<br>• • •<br>ሁሉም ሰው ታሪክ አለው። እርስዎ ዕድሜዎ ሲገፋ ታሪክዎ ምን እንዲሆን ይፈልጋሉ? የጉልምስና ዕድሜ ላይ በሚደረሱበት ጊዜ ታሪክዎ እንዲሆን የሚፈልጉትን ይናገሩ። | የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም የማባዛትና የማካፈል መልመጃዎችን እንዴት መስራት እንደሚችሉ ልጅዎ እንዲያስተምርዎ ያድርጉ። | ከእኛ በተሻለ ሁኔታ አምስቱን የስሜት ሕዋሳት የሚጠቀሙ እንስሳትን እንዲያስብ ለልጅዎ ፈተና ይስጡት። ዝርዝር ያውጡና ሌሎች ምሳሌዎችን ሲናገሩ በዝርዝሩ ላይ ይጨምሩ (ለምሳሌ፡ ውሾች ከሰው ልጅ በጣም በተሻለ ሁኔታ የመስማትና የማሽተት ችሎታ አላቸው)።<br>• • •<br>አንድ የፕላስቲክ ኳስ በተለያዩ ከፍታዎች ላይ በማንጠር ይህን ማድረጉ ኳሱ በሚነጥርበት ከፍታ ላይ (እና ከዚያ በኋላ የሚቆይበት ጊዜ ላይ) የሚኖረውን ውጤት ይታዘቡ። ልጅዎ በዚህ ተግባር እና በእምቅ የካይኔቲክ ኢነርጂ መካከል ትስስር እንዲፈጥር ይጠይቁ። | National Museum of the American Indian (በነጻ) ወይም ዲሲ ውስጥ የሚገኝ ብሔራዊ ፓርክን ይጎብኙና የዚህን አካባቢ ተፈጥሯዊ የመሬት አቀማመጥና ተፈጥሮ ለሰዎች ስለምታስገኛቸው ጠቀሜታዎች ከልጅዎ ጋር ይወያዩ።<br>• • •<br>የራሳቸውን ማንነቶች የሚያንጸባርቁ ሰዎችን ጨምሮ፣ በቅኝ ግዛት ስር በነበረችው አሜሪካ ይኖሩ የነበሩ የተለያዩ ሰዎች ሕይወትን በተመለከተ ልጅዎን ይጠይቁ። ሃገራችን፣ ሕዝባችንና ተቋማቶቻችን በጊዜ ሒደት ለሰዎች የበለጡ መብቶችን ለመስጠት እንዴት እንዳደጉ ከልጅዎ ጋር ይወያዩ። | በእያንዳንዱ ቀን በንባብ ላይ ምን ያህል ጊዜ እንዳሳለፉ መመዝገቢያ ያዘጋጁ! ከእያንዳንዱ ታሪክ የወደዱትን ገጸ ባሕርይ በመዘርዘር ገጸ ባሕሪው እርስዎ ያደነቁለትን ብቃት ያሳየበትን የታሪኩን ክፍል ይለዩ።<br>• • •<br>ብሔራዊ መካነ እንስሳትን ይጎብኙ! የሚወድዷቸውን እንስሳት ምልከታዎችን ይመዝግቡ (ቀለም፣ ቅርጽና መጠን)። ምልከታዎችዎ በተቻለ መጠን ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያድርጉ። ለምሳሌ፣ “አንበሳው ጠይምና ጠንካራ ነው።” |
| **የክረምት ወቅት** | Paul Revere እንግሊዞች በፈረስ ጀርባ እንደሚመጡ አስጠንቅቆ ነበር። እንደ Paul Revere ያሉ የማስጠንቀቂያ መልዕክትን በ Facebook፣ በጽሑፍ መልዕክት፣ Twitter ወይም Instagram ላይ ይጻፉ። የዚህ ልዩነት ምንድን ነው? | በተጨባጩ ዓለም ውስጥ ያሉ ክፍልፋዮችን ፈልገው ይለዩ። ልጅዎ መለኪያ ማንኪያዎችና መለኪያ ኩባያዎችን በመጠቀም የተለያዩ ክፍልፋዮችን መጠን በተመለከተ ምልከታና ንጽጽር እንዲያካሂድ ያድርጉ።<br>• • •<br>በሽያጭ ማስታወቂያዎች ውስጥ ክፍልፋዮችና ዴሲማሎችን ይፈልጉ። ልጅዎ ዴሲማሎችን ወደ ክፍልፋዮች፣ እንደዚሁም ክፍልፋዮችን ወደ ዴሲማል እንዲቀይር ያድርጉ። | ልጅዎ ከቴሌቪዥን ወይም ከተንቀሳቃሽ ስልክ (ወይም ኮምፒዩተር/ታብሌት መሳሪያ) ውጭ መኖር ይፈልግ ወይም አይፈልግ እንደሆነ ይጠይቁት። የአንዱ መኖር ከሌላው መኖር አንጻር ስላሉት ጠቀሜታዎችና ጉዳቶች ተወያዩ።<br>• • •<br>ስለ ቀጣዩ የ “ቢሆን” ምናባዊ ታሪክ ከልጅዎ ጋር ተወያዩ፡ በነገው ዕለት የመሬት መንቀጥቀጥ እንደሚከሰት ከተተነበየስ? ምን ያደርጋሉ? እርስዎና ቤተሰብዎ ምን ዓይነት እርምጃዎች ትወስዳላችሁ? የመሬት መንቀጥቀጥ ወይም ሌላ የተፈጥሮ አደጋ ቢከሰት የአደጋ ጊዜ ዕቅድ እንዲያወጡ ያድርጉ። | በልጅዎ ዕለታዊ ሕይወት ውስጥ ያሉ ነገሮችን መንስኤና ውጤት በተመለከተ፣ እንደዚሁም በአውዱ መሰረት ውጤቶች እንዴት እንደሚቀያየሩ ተወያዩ። | የ American History Museum’s Gunboat, Philadelphia ኤግዚቢት ይጎብኙ። ከዚያም ፊላደልፊያን ያሰጠመውን ውጊያ በተመለከተ የራስዎን ስእል ይሳሉ። ለተጨማሪ መረጃ americanhistory.si.edu ይጎብኙ።<br>• • •<br>ዘወትር ማክሰኞ Smithsonian Museum of Natural History’s Butterfly Pavilion በነጻ መጎብኘት ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ mnh.si.edu ይጎብኙ። |
| **የፀደይ ወቅት** | የ Smithsonian Museum of Natural History ይጎብኙ። እዚያ እያሉ፣ አለቶችና ማዕድናትን በተመለከተ የሚታዩ ነገሮችን ያስሱ። ሁለት የተለያዩ አለቶች/ማዕድናትን ይምረጡና ተመሳሳይነትና ልዩነቶቻቸውን ያጥኑ። ከዚያ፣ እነዚህ አለቶች/ማዕድናት እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ይወስኑ። ምናልባት ለጌጣጌጥ መስሪያ? ምናልባት ለግንባታ? | በተጨባጩ ዓለም ውስጥ ያሉ ማዕዘናትን ይለዩ። እነዚህን ማዕዘናት አኪዩት፣ ቀጥተኛ ወይም ኦብቲዩስ በማለት ይለዩና በማዕዘን ልኬት ላይ ምክንያታዊ የሆነ ግምት ይውሰዱ። | ልጅዎ “እኛ ሕዝቦች” የሚለውን አራት ደቂቃ የሚፈጀውን ተምሳሌታዊ የኮንግረስ ምስክርነት በቃል እንዲያጠና በማድረግ ለ ተምሳሌታዊ የኮንግረስ ችሎት እንዲዘጋጅ የሚያግዘውን ተከታታይ ጥያቄዎች ይጠይቁ። | | National Cherry Blossom Festival bit.ly/DCPSCherry ይጎብኙ።<br>• • •<br>ሰዎች አካባቢን ያገዙበትን ወይም የጎዱበትን ወቅታዊ ክስተት በተመለከተ ተነጋገሩ። ባህሪው ለወደፊት በሰዎች ላይ ስለሚያሳድረው ተጽእኖ ተወያዩ። |

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት · ሒሳብ · ሳይንስ · ማህበራዊ ሳይንስ · የማበልጸጊያ ተግባር